የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፺፰
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 98
ADDIS ABABA, 3rd August , 2016

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፫/፪ሺ፰ ዓ.ም

ለኤሌክትሪክ መረብ ማጠናከሪያና ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ተጨማሪ ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ…............................ገጽ ፱ሺ፩፻፹፰

**CONTENT**

Proclamation No. 973/2016

International Development Association Additional Financing Agreement for Electricity Network Reinforcement and Expansion Project, Ratification Proclamation......................................................Page 9188

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፫/፪ሺ፰

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ ልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለኤሌክትሪክ መረብ ማጠናከሪያና ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፩፻፵፪ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ አርባ ሁለት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የተጨማሪ ብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ ልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፦

## PROCLAMATION No. 973/2016

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS**, Additional Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit in an amount of 142,000,000 SDR (one hundred forty two million SDR) Special Drawing Rights for financing Electricity Network Reinforcement and Expansion Project was singed in Addis Ababa on the 15th day of June , 2016.

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 7th day of July,2016;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with of Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " ለኤሌክትሪክ መረብ ማጠናከሪያና ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው ተጨማሪ ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፫/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5814-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፵፪ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ አርባ ሁለት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation maybe cited as the "International Development Association Additional Financing Agreement for Electricity Network Reinforcement and Expansion Project Ratification Proclamation No. 973/2016.

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Credit number 5814-ET signed on 15th June 2016 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of 142,000,000 SDR (One hundred forty two million SDR) Special Drawing Rights in accordance with the terms and conditions set forth in the financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of August, 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**